
# ኢትዮጵያ

ግንቦት 2008 ዓ ም

ሙሉጌታ መንገሻ
የሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ
አህጉራዊ ኮሚቴ አባልና
ጸሐፊ የነበረና በህመም

## ልዩ እትም

## እንኳን ለ 44 ኛዉ ዓመት የኢሕአፓ ምሥረታ በዓል አደረሳችሁ

ርእስ አንቀጽ


ገፅ 2
እስከ ድል ያለዉን ርቀት ፤ በትግልና በዓላማ ጽናት!

//

ገፅ 3

ምን ይሰማ....... አገር

//

ዜናዎች ገፅ 4

//

ትናንትና ገፅ 5
በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

//

ነጻ ሀሳብ ገፅ 6
ከህዝብ ውጭ ስልጣን አይገኝም! ቢገኝም አይረጋም!

ታጥቦ ጭቃ--ቢከፍቱት ተልባ





እንኳን ለኢሕአፓ 44 ኛ ዓመት የ ምስረታ በዓል አደረሳችሁ። ኢሕአፓ ሲመሰረት አንግቦ የተነሳበት ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ በትግል እውን እንደሚሆን ተስፋ አለኝ

ገነት ግርማ
ተወዳጇ ነባር የኢሕአፓ




ከልጅነቴ ጀምሮ የማዉቀዉና የማከብረዉ በኢትዮጵያነቱ ፀንቶ የቆየዉ የነአይበገሬ ቤት የሆነዉ ኢሕአፓ 44 ኛዉን የምስረታ በዓሉን ሲያከብር ማየት መቻሌ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል! እግዚአብሔር ይመስገን። እንኳን ለ44ኛዉ አደረሳችሁ። የመጪዉን ዓመት በዓል በዉዷቷ አገራችን

ጠለላ ከበደ (እዉቋ አርቲስት




"በኢትዮጵያና በሕዝቧ የፀና ፍቅር ላይ በተመሰረተ ቃል ኪዳኑ ፀንቶ ፤ሀገራዊ ጥቅሟን እያስጠበቀ ፤ለማይቀረው ድል መብቃት፤ የኢሕአፓ መሠረታዊ ዓላማ ነው ። ለፓርቲው አባላት ደግሞ ፤ ለሕዝብ የገቡትን ቃለ- መሃላ ጠብቀው ፤ መሥዋዕት እየከፈሉ ማለፍ፤ ህያውነት እንደሆነ አምነው እስከ መጨረሻው ይታገላሉ ። በትግል መሞት ህይወት ነውና ! " በአባላቱ መሥዋዕት፤ ኢትዮጵያም የድል አክሊል ትጎናፀፋለች !
44ኛውን ዓመት የፓርቲ ልደት በዐል የምናከብረው፤ ይህንን ፅኑ ዕምነት መሠረት አድርገን ነው ። የትግላችንም ፤ አልፋ- ዖሜጋ ይኸው ነው ! "

ተገኘ ሞገሰ (የኢሕአፓ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል)



የኢሕአፓን 44ኛ ዓመት ስናከብር ድርጅቱ ስንቱን ጋሪጣ አልፎና ቃት ተቋቁሞ እዚህ መድረሱን፤ በጽናት ትግል መቀጠሉን ብቻ ሳይሆን ሀገራችን ኢትዮጵያ ራሷ ለረጅም ዓመታት በግፈኛ ገዢዎች የደረሰባትንም ስቃይ የምናስታውስበት ይሆናል ። አልፎም ለሀገርና ለሕዝብ ሲሉ ውድ ህይወታቸውን የሰዉትን፤ በውድቅት የተረሸኑትን፤ የፋሺስቶችና ጠባቦች ሽብር ሰለባ የሆኑንትን ሁሉ የምንዘክርበት ይሆናል ።ኢሕአፓ የውጭም የውስጥም ጠላቶችና አንጃዎችን እየተቋቋመ ትግሉን የቀጠለ ቢሆንም የ ጸረ ኢትዮጵያኖች የጋራ ጥቃት አሁንም እየተሰነዘረበት ነው ። ድርጅቱ ህልውናውን ጠብቆ መታገሉ ለህዝብ ሲጠቅም እንደቆየው ሁሉ አሁንም የኢሕአፓ ህልውና እንዳይነካ ሁሉም ዘብ ሊቆምለት የሚገባ ሆኖ ይገኛል ። ወያኔ እየተንገዳገደ ባለበትና የሕዝብ ጠላቶች ሁሉ ድሉን ሊቀሙት ባቆበቀቡበት ሁኔታ ኢሕአፓን በጋራ ጥረትና ሰፊ ድጋፍ ማጠናከር ወሳኝ ነውና ከድርጅቱ ጎን እንድትቆሙ፤እንድትሰለፉ ጥሪ አደርጋለሁ ።
"

ኢያሱ ዓለማየሁ (የኢሕአፓ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል)



"የኢሕአፓ አባላት ድርጅቱን የመሰረቱቱና ለረጅም ዓመታት በትግል እንዲቆይ ያደረጉት የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን የሚያስጠብቅበት፣ እኩልነትና አንድነቱ የሚያረጋግጥበት፣ አገራችንም ሉዓላዊነቷን ጠብቃ የበለጸገችና የተከበረች አገር የምትሆንበት ሁኔታ ለመፍጠር የትግል መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል እንጅ የስልጣን መወጣጫ፤ የግል ጥቅም ማዳበሪያ፤ የጎሳ ወይም የዘር መለያ፤ ወይም የጥላቻ ማስፋፊያ ርካብ ወይም መሰላል እንዲሆን አልነበረም። ለዚህም ነበር ብርቅዬ የኢሕአፓ አባላት ውድ የሆነ ህይወታቸውን የሰጡት፤ በየእስር ቤቱ የማቀቁት፤ ለስየልና ለስቃይ ሳይንበረከኩ ኢሕአፓ ያቸንፋል ብለው ህይወታቸውን የሰጡት፤ የሞቀ ቤታቸውን፤ ቤተሰባቸውን ስራቸውንና ንብረታቸውን ጥለው ወደ በረሃ የተሰደዱት፤ ለረጅም ዓመታ ትግሉን የሙጥኝ ብለው የታገሉትና እየታገሉ ያሉት። ኢሕአፓ የተመሰረተበትም ሆነ ሲታገልበት የቆየው ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ ከ44 ዓመታት በኋላ አሁንም ገና እውን ያልሆነ በመሆኑ ብዙ ውጣ ውረዶችና መሰናክሎችን ያለፈው ድርጅት አሁንም ህልውናውን ጠብቆ የጀመረውን ትግል ይቀጥላል። በዓለማችን ለአገርና ለወገን ራስን አሳልፎ ከመስጠት በላይ ክቡር የሆነ ነገር ባለመኖሩ ወጣቱ ክፍል የኢሕአፓን አርማና አላማ ተረክቦ ድርጅቱን እስከወዲያኛው ህልው አድርጎ እንደሚያቆየው ተስፋችን ከፍተኛ ነው።"

ፋሲካ በለጠ (የኢሕአፓ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል)


የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

EPRP.COM
ASSIMBA.ORG
DEBTERAW.COM
ወዘተ.

- FACE BOOK (ethiopianewspaper)

# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል**
**የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ**


5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com



**የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ የሳተላይት መስመር**

Channel Name : Finote Democracy
Satellite : Telstar
Azimuth : 15 deg West
Frequency : 12.550 MHz
Polarity : Horizontal
Symbol rate : 4411
FEC : 2/3


## ርዕሰ አንቀጽ

### እስከ ድል ያለዉን ርቀት ፤ በትግልና በዓላማ ጽናት!

የሕዝብ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባትን ዴሞክራሲያዊ ሀገር የመፍጠር ታላቅ ህልም የነበረዉ ወጣት ትዉልድ ካቀጣጠለዉ የትግል እንቅስቃሴ አብራክ የተወለደዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እነሆ ፵፬ (አርባ አራት) ዓመት ሞላዉ ። ይህ በራሱ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ በዘመናዊ የፖለቲካ ተቋማዊ ህልዉና ፋና ወጊ ለሆነዉ ለዚህ አንጋፋ ድርጅት ግዙፍ ታሪካዊ ክዋኔ ነዉ ።

በወቅቱ ፤ የኢሕአፓ ምስረታ እንደዛሬዉ በቀለም ብርሃን (ርችት) ቀንጅቶ በሰበር ወሬነት ለመበሰር አልታደለም ። ሆኖም ዜናዉ አድማሳትን አቆራርጦ በተሰማበት ጊዜ፤ ከአስገባሪዉ ሥርዓት ደይን ዉስጥ በየሥፍራዉ ትግል ላይ ለነበሩት አብዮታዊ ወጣቶችም ሆነ አሳር ፍዳዉን ሲቆጥር ለነበረዉ ተረጋጭ ሕዝብ ብሩህ ተስፋን ያዘለ ትልቅ የምስራች ሊሆን በቅቷል። ዛሬም ቢሆን ፤ በተሞክሮ የበለጸገዉና ማልዶ ያነሳዉን የትግል ዓርማ በሺህዎች በሚቆጠሩ አባላቱ የመሥዋዕት ደም ያቀለመዉ፤ የጎልማሳዉ ኢሕአፓ በዓለ ልደት በብዙሃን ኢትዮጵያዉያን ዘንድ የአልበገር ባይነት ተምሳል ፤ ወያኔያዊዉ አገዛዝ ለሚገረሰስበትና ለማይቀረዉ ሕዝባዊ አቸናፊነት አመላካች ኮከበ ጽባህ ነዉ።

ለኢሕአፓ የአርባ አራት ዓመታት ትግል ሻማዎችን ስንለኩስ፤ በትግሉ ርዝማኔ ዉስጥ በዜጎቻችን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ላይ የተከተለዉን እመርታ በኩራት እናስታዉሳለን። የየካቲቱን አብዮት ተከትለዉ የመጡትን፤ ንጉሣዊዉንና ወታደራዊዉን አገዛዞች ለማስወገድ የተደረጉትን ግብግቦችና ኢሕአፓ በበኩሉ በመሪነት የተጫወተዉን ታሪካዊ ሚና በአንክሮ እንዘክራለን ። ከትናንት እስከዛሬ በተዘረጋዉ ድርጅታዊ ታሪክ ዉስጥ ካፈራናቸዉ ጓዶች በትግሉ መስመር በጽናት ቆመዉ መስዋዕት የሆኑትን፤ ከዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይና ከጸገየወይን ገ/መድኅን (ደብተራዉ) አንስቶ የሚሰደሩትን የፓርቲዉን የአመራር አባላት፤ በወጣቱ ክንፍ (ኢሕአወሊ)፤ በላባደሩ (ኢላአማ)፤ በሠራዊቱ (ኢሕአሠ) ፤ በሴቶች (ኢሴትድ) ፤..... ወዘተ ስር በመሰለፍ ታግለዉ የወደቁትን የሕዝብ ልጆች በሙሉ በአርምሞ እናስባቸዋለን። የታገሉለት ዓላማ ዛሬም ህያው መሆኑን በአጽንዖት እንፈክረዋለን።

የምንገኝበት ወቅት፤ ሃያ ሚሊዮን ወገኖቻችን በረሃብ በትር ክፉኛ እየተመቱ የሚገኙበት፤ ጋምቤላ ዉስጥ ደግሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት የተቀጠፈበትና ሕጻናት ሳይቀሩ ታፍነዉ የተወሰዱበት ነዉ ። ወያኔያዊዉ ዘረኛ ቡድን ከጫካ ዕድሜዉ አንስቶ በሕዝብ ችግርና ጉስቁልና መነገዱና ማትረፉ ተመስክሮለታል ። ብሔራዊ ዉርደት የአገዛዝ ዘመኑ ልዩ መታወቂያ መሆኑንም ጠንቅቀን የምናዉቀዉ ነዉ። ኢትዮጵያችን ፍጹም ዘረኛና አምባገነናዊ በሆነ አገዛዝ ሥር ወድቃለች። አፈና፤ እስራትና ግድያ የተለምዶ ግብር በሆኑበት ድቅድቅ ጽልመትም ተዉጣለች ።

ረገጣ ባለበት ሁሉ ለመብት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ የሚደረግ የሕዝብ ትግልና እንቅስቃሴ መኖሩ የግድ ነዉ። በመሆኑ በአራቱም ማዕዘናት የአገዛዙን ዕድሜ የሚያሳጥሩ አመጾች ምልክታቸዉን አሳይተዋል። የዚያኑ ያህልም፤ የወገኖቻችን ከኑሮ መፈናቀል፤ ስደት፤ እሥራትና ግድያ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በሕዝብ ላይ የሚደርሰዉ ወያኔያዊዉ ግፍና በደል የአገዛዙ አቋም በሕዝቡ ትግል ይበልጥ እየተናጋ በሄደ መጠን እየተባባሰ እንጂ እየተለሳለሰ አይመጣም። ከተግማማዉ ሥርዓት ዉድቀት በፊት በአገራችን ህልዉና ላይ ከተደቀነዉ አደጋም ሆነ በሕዝቧ ህይወት ላይ ከተጋረጠዉ መራር ዕጣ የሚገላግል አንዳችም መድኅን አይገኝም።

ኢሕአፓ ፤ የተገፈፈዉ የሕዝባችን መብት፤ የተሸረሸረዉ የሀገር ክብርና ቀዳሚዎቹ ትዉልዶች ወጥተዉና ወርደዉ ያወረሱን አኩሪ ታሪክና ባህል በሚኮሰኩሳቸዉ ከሀዲዎች የሚዘመትበት ኢትዮጵያዊነት ከትግል በቀር የሚታደገዉ ሌላ መላ እንደሌለ እምነቱ ነዉ ። አንዱን አገዛዝ ጥሎ በሌላዉ ለመተካት በታሰበ አጭር ህልም አይደለም። ሕዝቧ የሥልጣን ባለቤትነቱ የተረጋገጠባት፤ ፍትህ፤ መብትና እኩልነት የማይዛነፍባት ፤ ታፍራ የተከበረች ኢትዮጵያ ዕዉን እስከምትሆንበት የድል ዕለት ድረስ ለመታገል ከዛሬ ፵፫ (አርባ ሦስት) ዓመታት በፊት በቃል ኪዳን የታተመ ታሪካዊ ኃላፊነትን ተቀብሎ የዘለቀ ድርጅት ነዉ ። የዚህን ቀዳሚ ድርጅታዊ መርህ ታላቅነት በሺህዎች የሚቆጠሩ አባላቱ የሥቃይና የህይወት ዋጋ በከፈሉበት መሥዋዕት አስከብረዉ እስከዛሬ አዝልቀዉታል ። በዘረኛዉ ቡድን አይዞህታና ከአገር በተዘረፈ ሀብት ከታጨቀ ካዝናዉ ቀለብ የሚሰፈርላቸዉ ቅጥረኞች ወርቃማ ታሪኩን በአሉታ ሊያጠለሹት የተቅበዘበዙትን ያህል ፤ ኢሕአፓ በፍቅርና በክብር ከሕዝብ ልብ ቦታ ያገኘ ድርጅት መሆኑን መደለዝ አልተቻላቸዉም።

አባላቱና ደጋፊዎቹም ፤ በድርጅታችን የምሥረታ በዓል አጋጣሚ፤ በትግልና በማይናወጥ የዓላማ ጽንዓት፤ እስከ ሕዝባዊዉ ድል ብሥራት ያለዉን ርቀት ለመዝለቅ ለሀገርና ለወገን በፍቅርና በክብር የገባነዉን የቃል ኪዳን እናድሳለን።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግላችን ያቸንፋል!
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!

# ምን ይሰማ......አገር?



**" የኢህአዴግ መሪዎች ፤ ከንጉሡም ከደርግም ተምረዉ ከሌሎች ኃይሎች ጋር ብሔራዊ መግባባት ፈጥረዉ ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለመታደግ የፖለቲካ ቁርጠኛነት ማሳየት ይኖርባቸዋል ።"**

*(መረራ ጉዲና (ዶ/ር) በአሜሪካ ሊያቀርቡት ነበር በተባለ ጽሁፍ የታዘለ ሃሳብ ፤ ዘሐበሻ ድረ-ገጽ ኤፕሪል ፲፪ እንዳሰፈረዉ፤)*

- **ወይ የፖለቲካ ሳይንስ !.... ፖለቲካዉም ፤ ሳይንሱም፤ (ከነአስተማሪያቸዉ) አብደዉ መሆን አለበት ። ይህን መሳይ ይዘት ያለዉ ወረቀት ተይዞ የአትላንቲክ ዉቅያኖስን ለማቋረጥ ትኬት ይገዛል ?! ....እዚያዉ-ከአፍንጫዎ ስር ... በአንድ ታክሲ ርቀት ካለዉ ፓርላማ ወረድ ብለዉ ቢያነብቡላቸዉ ካቦዉ አባዱላና ክቡራን እስረኞቹ በታላቅ ጭብጨባ ይቀበሉዎም አልነበር?!**

//

**"ያልኩትን በደንብ አስታዉሳለሁ ።...ኢሳያስ ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ ይፈልግ ነበር የሚለዉን ሽንጤን ገትሬ እከራከራለሁ ብያለሁ።እነሌንጮ ለታም በናንተ ቴሌቪዥን አማካይነት እኔ ያልኩትን የሚመሰክር መግለጫ ሰጥተዋል ።"**

*(ካሳ ከበደ፤ በኢሳት ትዩብ ኤፕሪል ፳፫ ከተናገረዉ የተቀነጨበ)*

- እረ እኛም አንዘነጋዉም ። " ሰይጣን ለብልሃቱ ከመጽሀፍ ይጠቅሳል፤" የሚለዉን የቆየ አባባል ፤ " የኢሡፓ ዋሾ ቢቸግረዉ - አነግን ነቃሽ ቆጠረዉ" በሚል ጊዜያዊ ብሂል ተክተነዋል ። "የተረት ስልጡን የለዉም፤" ሲባል አልሰምተንም።

//

**" የሕዝቡ አብዮት ተነጠቀ የሚለዉ ትክክል አይደለም ።"**

*( አሰፋ ጫቦ በአዉስትራሊያዉ ኤስ ቢ ሲ ሬድዮ ፤ ማርች ፲፩ ፪፻፲፰ ካካሄደዉ ቃለ ምልልስ የተወሰደ፤)*

- **ድሮስ የነጣቂዎቹ አባሪ ተባባሪዎች ከዚህ ሌላ ምን እንዲሉ ነበር የጠበቅከዉ ቼንቶ ?!.... ጠያቂዉን መጠየቅ አይምሰልብንና " የሕዝብ ....." የሚለዉ ቃል ባለቤትነትን አያመለክትምን ?!**

//

**" አንድ ነገር ልንገራችሁ ፤ ..... ቆይ.... በኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ትልቅ ነጋዴ እቤቱ ዉስጥ እስር ቤት አለዉ ሲባል ታምናላችሁ ?"**

*(ጠቅላይ ተብዬዉ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ተመርጠዉ ለተጠሩለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁራን ከተናገረዉ፤)*

- ***ምስጢር ተነግሮ ተሙቷል ! አንተ ከምታዉቀዉ በላይ ሕዝባችን እጅግ ብዙ የወያኔ ጉዶችን አሳምሮ ያዉቃል ። ማሰርያም መግደያም ቦታ ያላቸዉ እነዚህ ፈላጭ ቆራጮች ግና አንተ እንዳልከዉ ተርታ ነጋዴዎች ሳይሆኑ ንግዱን ተግነዉ ያደፈጡ ቀንዳም ወያኔዎች መሆናቸዉን እንነግርሃለን።***

//

**"እንዷት እህታችን አክቲቪስት ስለሆነች freedom of expression ለመገደብ ብሎ ነዉ ያሰረዉ ተገቢ አይደለም ብለዉ በሪፖርተራቸዉ አወጡ። ....ነጻ እናዉጣዉ ብለን ወጣ ፤ ( ጾታ አልገልጽም ።) .... ከዚያ በኋላ ራሳቸዉ ትኬት ገዝተዉ ዋሺንግተን ዲሲ ወሰዷት ። በነጋታዉ በቴሌቪዥን ላይ ወጣና " እኔ እኮ ጀግና ነኝ ፤....፤" አለ ።"**

*( ጠቅላይ ተብዬዉ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ፤ ለአአዩ ምሁራን ከተናገረዉ ፤)*

- *የቋንቋ አጠቃቀምህን ግድፈት ብንነቅስ " ብሔር- ብሔረሰብ - ሕዝቦች" በሚሉት ለማዳ የሰበብ ሽንቁር ለማምለጥ ማኅንበስህ አይቀርምና እንለፈዉ ። የገዛ ምራቅህ ትን እስኪልህ የምታኝኀደጉደዉ ሙት-ኮራጅ የአነጋገር ስልት ለዚህ ተራ ስህተት የዳረገህ መሆኑን ግን እንጠቁምሃለን። ሌላዉ ቢቀር ወያኔ ሲቀር ለሚተርፈዉ ዘመንህ ያገለግልህ ይሆናል።*

//

**" በቀጥተኛ መንገድ ሲታይ ደግሞ ፤ (ኢሕአፓ) የቀድሞ ኢህዴን የአሁኑ ብአዴን ተተክቷል የሚል እምነት አለኝ ። እነ በረከት ስምዖን፤ ጎላዌ ዮሴፍ፤ ገነት ዘዉዴ፤ አዲሱ ለገሰ፤ ወዘተ....የዚህ አኩሪ ህዝባዊ ተጋድሎ ወራሾችና አስቀጣዮች ናቸዉ የሚል እምነት አለኝ ።"**

*( ታደለ አብርሃም ኤፕሪል ፳፯፤ በኢትዮ ሚድያ ድረ-ገጽ)*

- **ወያኔ ፈጠራዋ ሁሉ ነጥፎባት የቀድሞ ትፋቷን ቃራሚ ሆና አርፋዋለች ። የዛሬን አያድርገዉና፤ ፓስተር ነኝ ባዩ፤ የወያኔ ጠቅላይ ወንጀለኛ ኢየሱሳዊ ከመባሉ በፊት ይህንኑ ቅርሻት በየአደባባዩ ደጋግሞ ሲያቀረሽ ባጅቷል።-የጅልኛ። ....እንዲያዉ ግን፤ በገንዘባችሁ ባሳተማችሁት መጽሀፍ ላይ እንኳ ከደራሲ ተብዬአችሁ ጋር መስማማት ያቅታችኋል ?! ትርጉሙ ከዘለቃችሁ ፤ " ዉሻ!! ምን አገባት እርሻ?!" በሚል እንለያይ።**

**" ...በየትኞቹም ድርጅቶች ዉስጥ በአሁኑ ጊዜ ያሉ በኛ ዘመን የነበሩ ሰዎች ጡረታ መዉጣት አለባቸዉ ብዬ ነዉ የማስበዉ ።.....ከአርባ ዓመታት በላይ የነበሩበት ቦታ ላይ ቁጭ ብለዉ የድርጅት አመራር ነኝ ብለዉ አሁንም ያንኑ አመራር ልስጥ ማለት በጣም ከባድ ነዉ።"**

*( ክፍሉ ታደሰ ከየመቶ አለቃ ካሳሁን ሰቦቃ ጋር በኤስ ቢ ሬዲዮ ሜይ ፲፪ ቀን ያደረገዉ ቃለ ምልልስ፤ )*

- **ብተናዉ አሁንም አላበቃለትም ማለት ነዉ ። አንድ ሰሞን ከወያኔ ጋር እንገፍ እንገፍ ማለትዎን ያስተዋሉ ሰዎች " አሁንስ ማረፊያ ተገኝላቸዉ፤" ማለታቸዉ በስህተት ኖሯልና!.... አዎን ፤ እነዚህ " ጡረታ ይዉጡ " የሚሏቸዉ አንጋፋ ታጋዮች በአመራር ላይ እስካሉ ድረስ ቀጣዩ ዙር የብተና ስልትዎ አይሠራም ። ደግሞም የኢሕአፓ ድርጅታዊ አሠራር የኢሕአፓዎች ጉዳይ ነዉ ።እናም አርፈዉ የ"ነበርኩ" ወሬዎን በየደረሱበት ቢሸከሽኩ ይቀልልዎታል። ሥራ አይፍቱ!**

//

**"ኢሕአፓን በሚመለከት ብዙ ኢሕአፓ የነበሩ ወዳጆቼ ድርጅቱ አመሠራረቱና አመራሩ በደንብ መፈተሽ አለበት፤ ይህ ማለት በቆራጥነት ለነብሳቸዉ ሳይሳሱ ለትግሉ ቆመዉ የነበሩትን መክዳት ሳይሆን፤ ትክክለኛ መድረሻዉ ግብ ሳይታወቅ ምናልባትም " የኤርትራን ነጻ ሀገርነት" ለማረጋገጥ በሚደረገዉ ጥረት የዉስጥ እሳት እንደሆኑ ወንድሞቻችን እህቶቻችን ተማግደዉ አለመሆኑ ይጣራ ስንል የሚሰማን አናገኝም። ሁሌም ስለ ኢሕአፓ ጀግንነት ተራራ አንቀጥቃጭ ትዉልድነት ብቻ ይነገር የሚል ስሜት አለዉ።"**

*( የቀድሞዉ የወያኔ ፓርላማ አባል ግርማ ሠይፉ " የአሰፋ ጫቦ " የትዝታ ፈለግ" መጽሀፍ እኔ እንደገባኝ በሚል ርዕስ በድረ ገጽ ያስነበበዉ መጣጥፍ፤)*

- **ጉድ እኮ ነዉ ፤ ከአገር አስገንጣዮቹ ጋር እየተሞዳሞድክና መለኪያ እያንጫለጥክ ነዉ ሌላ ተወንጃይ የምታነፈንፈዉ ?!.....ለነገሩ ዝንቦች በቆሻሻ ሥፍራ መተቃቀፋቸዉ አዲስ አይደለም። አስፋና ግርማም በማዕከላዊዉ የደርግ የማሰቃያ ገሃነም ሊቃነ ሰይጣናቱን ኮሎኔሎች ተስፋዬ ወ/ሥላሴንና አርጋዉ እሸቱን በመልካም ሰዉነት ስታንቆለጳጵሱ መታየታችሁ ከዚያ ዉጭ የሚነግረን ነገር የለም።" " የሱፍ አበቦች"ን ለሀሰት ክስህ ማጠየቅያ ስታደርግ ዓላማህን አራቁተኸዋል። የወያኔ ብር ከገዛዉ " ደራሲ" ልብ ከሃሰት ሌላ ምንም እንደማይወለድ ማንም ያዉቀዋል።**

## ፍካሬ ዜና
## አጫጭር ዜናዎች

(በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ የተላለፈ )

- የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች መተባበር ተስኗቸው ለሚገኙበት አሳዛኝና ጎጂ ሁኔታ በቅድሚያ ተጠያቂ ራሳቸው ናቸው ቢባልም ህብረት እንዳይመሰረት ዕንቅፋት የሆኑት ሻዕቢያና አሜርካ ናቸው ተባለ ። ይህን ያሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምገማቸውን ሲያብራሩ ሻዕቢያ የሀቀኛ ሀገር ወዳዶች ህብረት መመስረቱ ላለው ዕቅድ ጎጂ ነው ብሎ አምኖ በመቀጠሉ በኤኤፍዲ ምስረታ ጊዜ እንደታየው የህብረት ጥረቶችን በአቋራጭ ጠልፎ እየጣለና በህብረት ደጋፊነት ሽፋን ክፍፍልን እያስፋፋ ሲሄድ ቆይቷል ብለዋል ። የወያኔ ደጋፊ አጋር የሆነችውም አሜሪካ እንዲሁ የህገርን ሉ ዓላዊነት የሚያስከብር ሀገር ወዳድ ሀይል በኢትዮጵያ በስልጣን እንዲመጣ ስለማትፈልግ የሀገር ወዳዶችን ህብረት ከማደናቅፍና ለወያኔ ከመታደግ ወደኋላ ብላ አታውቅም በሚልም ትችት ቀርቧል ። አሜሪካ በተለይ በውጭ ሀገር ሆነ በውስጥ ሰላዮቿና ቅጥረኞቿን አሰማርታ ሀገር ወዳድ ሀይሎችን እየከፋፈለችና እያጠቃች መሆኑን በአሁኑ ጊዜ አሌ የሚል ብዙ ሰው የለም ሲሉ ተቺዎቹ አረጋግጠዋል ። ወያኔና አሜሪካን በመከተል የህብረት ጥረቶችን በዚህም በዚያም የሚያደናቅፉትን አስመሳይ ሀገር ወዳዶችና ተቃዋሚዎችም ሕዝብ እያደር ነቅቶባቸዋልም በሚልም መረጃ ተሰንዝሯል ።

- በቀይ ባሕር አካባቢ እየተካሄደ ባለው የጦር መሳሪያ ንግድ ኢራን፤ግብጽ፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ሻእቢያና ወያኔም አሉበት ተባለ። ባለፉት ወራቶች በርካታ ጀልባዎች መሳሪያ ጭነው ወደ ፑንትላንድና የመን ሲጓዙ መያዛቸውን ያጋለጡ ክፍሎች በሶማሊያ ውስጥ አል ሸባብ የተባለውን ጽንፈኛ ቡድን እንዋጋለን ከሚሉት የአፍሪካ ህብረት ሀይሎች ውስጥም ኬንያና ዩጋንዳ መሳሪያ ሲሸጡ መገኘታቸው ተጠቅሰዋል ። የኢራን መሳሪያ የሚላከው ለየመን ሁቲ አማጽያን ብቻ ሳይሆን በሶማሊያ ላሉም ጂሃዲስት ለሚባሉ ሀይሎች ነው ያሉ ክፍሎች ደግሞ ወደ ፑንትላንድ በብዛት እየመጣው ያለ የጦር መሳሪያ አንዱ ዋናው ምንጭ ወያኔ ነው ተብሎም ተጠርጥሯል ።

- በቅርቡ የባዕድ የንግድ ምክር ቤቶች በኢትዮጵያ መሬት ቢሮዎችን ከፍተው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል ህጎችን ወያኔ ሊያጸድቅ ነው ተብሏል ። የወያኔ ኤኮኖሚ ደቆ ባለበትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት በሰፈነበት ይህ እርምጃ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል የሚለውን ወያኔ እንዳልመረመረውና ደንታም እንዳልሰጠው ውስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ ።

- ከወያኔው አየር መንገድ ጋር ንትርክ የገባው የአሜሪካ ፐሪንስ ሰርቪስስ ኢንተርናሽናል ኩባንያ ለፐሬዚዳንት ኦባማ የተቃውሞ ደብዳቤ መላኩ ተነገረ። ፐሪንስ ሰርቪስስ ተቃውሞ ያሰማው የአሜሪካ መንግስት ምንም ድጋፍ ሳይሰጠው መቆየቱን በተመለከተ ሲሆን የወያኔ ወዳጅ የሆነችው ሂላሪ ክሊንተን የአየር መንገዱ ጠበቃ የሆነው ከሚካኤል አታዲካ የቅርብ ትውውቅ ያላት መሆኗንም አጋልጧል ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚባለው ተቋም በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር መግባቱና ከሰራተኞቹ ዘጠና በመቶ የሚሆኑት የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውና የወያኔ አየር መንገድ ይባል የሚሉ ክፍሎች አጋልጠዋል ።

- ወያኔ የሀገር ወደቦችን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ በጅቡቲ ሲጠቀም መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን ከሶማሊያ የተገነጠለችው የሶማሌላንድ ወደብን በርበራንም መጠቅም መጀመሩ ሲነገር ቆዩታል ። ጅቡቲ ወደቧን ለዱባይ አኮናትራ ብትቆይም በጅቡቲና ዱባይ መሃል በተነሳው ንትርክ ግንኙነታቸው ሻክሮ አሁን ደግሞ ዱባይ የበርበራን ወደብ ለመጠቀም የ 30 ዓመት ፍቃድ፤ሊዝን ወስዳለች ተብሏል ። ወያኔ ይህን ሁኔታ--እንደ አልጄርሱ ስምምነት--ድል ና ጠቃሚ ብሎ ሊያቀርብ ደፋ ቀና እያለ መሆኑን የነቀፉ ክፍሎች የሳውዲና የካታር ወደ ኢርትራ በጦር ደረጃ ሳይቀር መግባት፤ ግብጽ አሁንም ኢላማዋን ያልቀየረች ሆና ባለበት በርበራ ላይ የዱባይ/የአረብ ቁጥጥር መስፈኑ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት ሳይሆን ከበባውን የሚያጠናክርና የሚጎዳት ይሆናል ሲሉ ታዛቢዎች ገምግመዋል ። ይህ በዚህ እንዳለ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኔታናሁ በሐምሌ ወር ኢትዮጵያን ይጎበኛል ተብሏል ።

- ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ለወያኔ ፓርላማ ማክሰኞ ግንቦት 9 ቀን 2008 ዓ.ም. ባቀረበው ሪፖርት ላይ ከዓመት ዓመት የገንዘብ መባከንና የንብረት ዘረፋ እየተካሄደ መሆኑን አመልክቷል። ለገንዘብ ብክነቱ እንዲያመች የገንዘብ ክፍያዎች በአብዛኛው የሚፈጸሙት የሂሳብ አሰራርን በጣሰ መልኩ እንደሆነ ተገጿል። በዚህ መሠረት ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል። በሂሳብ አሰራር ያልተወራረደ የሚባል ሂሳብ የተዘረፈ ማለት እንደሆነ ከፍተኛ የሂሳብ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። በሪፖርቱ ላይ ከተገለጹት ጉዳዮች መሀል የወያኔ ሹመኞችን አረመኔነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎችን ለአርሶ አደሮች እየሸጠ መሆኑ ነው። በተመሳሳይም የአምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ብር ግምት ያላቸው መድሀኒቶች በመድሀኒት ፈንድ አቅርቦት መጋዘን ውስጥ መገኘታቸው ተጨማሪ ዘግናኝ ጉዳይ ሆኗል። መድሀኒቶቹ የተቀመጡት አዲስ ከሚገቡ መድሀኒቶች ጋር እየተመሳጠሩ ሊታደሉ እንደሆነ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ያስረዳሉ። በርካታ ንብረትም እንደተዘረፈ በሪፖርቱ ተጠቅሷል። በኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲቲዩት ስም ከተመዘገቡ መኪናዎች አስሩ መዘረፋቸው በሪፖርቱ ተጠቁሟል። ይህ ድርጊት መሬት ውስጥ እንደሚባሉት የጠፉት ሰማያ ስምንት የኮንዶሚኒየም ህንፃዎች ዓይነት መሆኑ ነው። በዚህ ዘረፋ ላይ ግንባር ቀደም የሆኑት ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የትምህርት ሚንስቴር፣ ምርጫ ቦርድ፣ መከላከያ ሚንስቴር፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ወላታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህር ዳር የኒቨርሲቲ፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ሲሆኑ በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎቹ የዘረፋ ተቋማት እንደሆኑ ሪፖርቱ ያሳያል። በተመሳሳም አብዛኛዎቹ ሆስፒታሎችም በዘረፋ የተጨማለቁ እንደሆነ ከሪፖርቱ መረዳት ተችሏል።

- ከሚያዚያ ወር አጋማሽ አንስቶ የጎርፍና የመሬት መንሸራተት አደጋ በሰው፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እደረሰመሆኑ በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወቃል። በጅጅጋና በድሬዳዋ የተከሰተው የጎርፍ አደጋ በመላው አገሪቱ እየተዳረሰ መሆኑን ከየአካባው ከሚደርሱን መረጃዎች መረዳት ችለናል። እስካሁን ወደ 200 ሰዎች በጎርፍ አደጋ ብቻ ህይወታቸውን እንዳጡ ከሚደርሱ መረጃዎች ተገንዝበናል። በወላይታ የደረሰው የመሬት መንሸራተት ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል ስጋት አለ። በዋና ዋና ከተሞች አደጋ ቢደርስ ይህን ለመከላከል የተዘጋጀ አቅም ያለው ተቋም አለመኖሩም በዚያው ልክ ተጋልጧል ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-4217
ኢሜል፡ espic@aol.com
ፖስታ፡ EPRP
P.O. Box 73337
Washington, DC. 20056
ድረ ገጽ፡ eprp.com

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል
ስልክ፡ (202) 291-5832
ኢሜል፡ eprpylnew@gmail.com
ፖስታ፡ EPRPYL
5309 Georgia ave.
Washington, DC. 20011
ድረ ገጽ፡ eprpyl.com

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

### 4

መርካቶ ላይ የተወሰደዉ ፋሺስታዊ ርምጃ ያልተጠበቀ አልነበረም ። ሆኖም ከርምጃዉ ስፋትና ርምጃዉ ላይ ከተሰማራዉ ኃይል ጭካኔ አንጻር ሲታይ ግን ድንገተኛነቱን መካድ አይቻልም። ወደማዕከላዊዉ የመገበያያ ሥፍራ የሚወስዱትን ጎዳናዎች በሙሉ በታንኮች ከዘጉ በኋላ ያላቸዉን ኃይል ሁሉ በማሰለፍ በዙሪያ ክብ ቀለበት ዉስጥ አስገቡት። ቀጥሎም ማንኛዉም ተግባርም ሆነ እንቅስቃሴ በኃይል እንዲገታና ቀስበቀስ እንዲቆም ተደረገ። በተደጋጋሚ ለመፈተሽና በነፍሱ ላይ ቁማር ለመጫወት የፈቀደ ሰዉ ካልሆነ በቀር ማንኛዉም ሰዉ በየመንገዶቹ ከተቋቋመዉ ከእያንዳንዱ ኬላ መራቅ ወይም ከሥፍራ ወደ ሥፍራ የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ መግታት ነበረበት ።

በዚያ የመርካቶ ምስቅልቅል ዉስጥ ፤ አሳሾቹ ጋት በጋት ወደፊት እየገፉ በሄዱ ቁጥር ብረት ለበሶቹ ተሽከርካሪዎቻቸዉ በሺህዎች የሚቆጠሩትንና ከካርቶን ፤ከአስፋልት ሬንጅ በርሜሎች ፤ ከቆርቆሮና ከፕላስቲክ የተሠሩ ዉትፍትፍ ሱቆችና የችርቻሮ መደቦች ዳመጧቸዉ ። ዕድሜ ልክ የተጠረቃቀመዉን የመሀከለኛ ነጋዴዎችን ሀብት እና የለማኞችን መጠጊያና ንብረት እንዲያ ባለ ሁኔታ ማዉደማቸዉ ትንሽ እንኳ የሚሰቀጥጣቸዉ አልነበሩም። ትጥቅ ያልነበራቸዉ ነጭ ለባሽ ደኅንነቶች በአደገኛነት የተጠረጠሩትን ሥፍራዎች ለማነፍነፍ አካባቢዉን ሙሉ በሙሉ ወረሩት ።እነርሱን ደግሞ ከእግር እስከ ራስ የታጠቁና ገና አሰሳዉን ከመጀመራቸዉ ግራና ቀኙን በተኩስ ማናወጥ የጀመሩ የአሰሳ ቡድኖች ተከተሏቸዉ ። የባለ ነጥብ አርባ አምስት ኮልትና የባለ ነጥብ ሠላሳ ስምንት ሪቮልቨር ሽጉጦች እንዲሁም የኤ ኬ አርባ ሰባት (ካላሺንኮቭ ) ጠመንጃዎች በአጭርና በሩምታ ሲተኮሱ ይደመጥ ነበር ። ቀኑን ሙሉ ቀዉጢ ሆኖ ነበር የዋለዉ ። ታንኮቹ እንኳ ሳይቀሩ "ጠንካራ ምሽጎች" የተባሉትን መሸሸጊያዎች ለመደምሰስ ፤ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያህል ከጥቅም ላይ ዉለዋል ።

የሰዉ ደም እንደ ዉኃ የፈሰሰበት ዕለት ነበር ።በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የተረሸኑ ሲሆንከዚያ በላይ ቁጥር የነበራቸዉ ደግሞ ቆስለዋል ወይም ታስረዋል ። እርግጥ ነዉ ሙትና ቁስለኛዉ ከአንደኛዉ ወገን ብቻ የተቆጠረ አልነበረም። በርካታ ቁጥር ያላቸዉ የአሰሳዉ ቡድን አባላት ( ከፊሎቹ ከራሳቸው ላይ ጠላቶቻቸዉ ነጥቀዉ በተገለገሉበት መሳሪያ )ተገድለዋል፤ ቆስለዉማል ።

የመጀመሪያዎቹ ተኩሶች በተሰሙበት ጊዜ መርካቶን ከሚጎራበተዉ የተክለ ኃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ነበርኩ ። በጋዜጣ የተጠቀለለ ምግብና የሚበተኑ ወረቀቶችን የያዝኩበትን ዘንቢል በአፋጣኝ አስወገድኩት ። የመገናኛ ሥፍራ ማመስጠሪያዎች የሰፈሩባቸዉን አነስተኛ ብጣሽ ወረቀቶችን አኝኬ ተፋኋቸዉ ። ፊቴን አዙሬ በመመለስ ፈንታ ወደግርግሩ ሥፍራ መቅረብ የተሻለ ሆኖ ተሰማኝ ። አንድም ደግሞ የስሚ ስሚ መረጃ ከመቃረም ይልቅ እኔዉ ራሴ ስለሁኔታዉ ተጨባጭ የሆነ ዕዉቀት እንዲኖረኝ ፈልጌ ነበርና ሲኒማ ራስ አጠገብ በሚገኝ የስላች መንገድ አድርጌ ወደ አሰሳዉ ቀጣና ገባሁ ። ወዲያዉኑ በአካባቢዉ የሚተራመሰዉን ጠላት ለመመልከት በመቻሌ ዉሳኔዬ ያልሰከነና አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ተረዳሁ ።እናም እምብዛም "የዴሞዎች" ተደርጎ ወደማይገመተዉና በአብዛኛዉ የእጅ ሰዓቶችና የሙዚቃ ማጫወቻዎች የሚሸጡባቸዉ መደብሮች በመደዳ ወደሚገኝበት የገበያዉ ክፍል አፈገፈግኩ ። ከዚያም ፤

በመደረግ ላይ የነበረዉን ሁሉ ከርቀት ለማየት እንዲመቸኝ ፤ ብዙ ሰዉ ከሚሰባሰብባቸዉ የአዉቶቡስ ፌርማታዎች ከአንደኛዉ ዘንድ ተጠግቼ ቁጢጥ አልኩኝ ።

ተኩስ ከሚሰማባቸዉ ሥፍራዎች ጋር ሲነጻጸር የነበርኩበት ቦታ ሰላም የሰፈነበት ይመስላል ።ትንሽ ፈንጠር ብለዉ ከሚገኙትና በ"T" ቅርጽ ከሚጋጠሙት ሁለት አዉራ መንገዶች ላይ እስከ ተሲያቱ አጋማሽ የዘለቀ አነስተኛ እንቅስቃሴ ይታይ ነበር ። ከዚያ በኋላ እስረኞች የተጫኑ ማርቼዲስ እና አይፋ ሰራሽ የጭነት መኪናዎች በሦስትና በአራት እየተቧደኑ ያለማቋረጥ ያልፉ ጀመር ።ከፊሎቹ የጭነት መኪኖች የቆሰሉና ቁስላቸዉ በፋሻ የተጠቀለለ ግለሰቦችን ነዉ የተጫኑት ። ከቀትር በስትያ ረፋዱ ላይ ደግሞ የጭነት መኪናዎቹ ምልልስ እየጨመረ ሄደ ። አንድ የጭነት መኪና ሙሉ በደስታ የሚፈነጥዙ ደኅንነቶች "ታላቁን መሪ" ( አምባገነኑን መንግሥቱ ኃ/ማርያምን) የሚያወድሱ መፈክሮችን በጩኸት እያሰሙ ፤ አንድ "የተያዘ" ዑዚ ጠመንጃ እያሳዩና እየፎከሩ አለፉ ። የጸሀይ መጥለቂያ መቃረቢያ ላይ አንድ የታጣቂዎች ጭፍራ በዝግታ ከሚጓዝ የጭነት መኪና ላይ እየዘለለ ሲወርድ ተመለከትኩ ። ታጣቂዎቹም ጠመንጃዎቻቸዉን በሚያስፈራራ ሁኔታ በመወደር በቀጥታ ወደ አንድ የአሪስ ሰዓት መሸጫ መደብር ገቡ ። የሙስሊም ቆብ ያጠለቀዉ የሱቁ ባለቤትና ልጁ ሳይሆን እንደማይቀር የምገምተዉ ትንሽዬ ልጅ እጆቻቸዉን ከራሳቸዉ በላይ እንደሰቀሉ እየተገፈተሩ ወጡ። ከዚያም የታጣቂዎቹ ጭፍራ መደብሩን አሟጥጠዉ ከዘረፉና ከመሀከላቸዉ አንደኛዉ የመደብሩን ባለቤት በጠረባ መሬት ላይ ከጣለዉ በኋላ ከመጡበት መኪና ላይ እየዘለሉ በመዉጣት እብስ አሉ። መደብሮቻቸዉን ቀደም ብለዉ በመዝጋት በሥፍራዉ ያልነበሩቱ ባለሱቆችም ቢሆኑ ከዘረፋዉ አላመለጡም ። አሳሾቹ ቡድኖች የተዘጉትን ሱቆችና መደብሮች እየሰበሩ ይገቡ ነበር ።

የደህንነቶቹ ኃይል አካባቢዉን ለቅቆ መሄዱ ከታወቀ በኋላ የሚተራመሰዉ የሰዉ መዓት ቀስ በቀስ ጊዜያዊዎቹን የፍተሻ ኬላዎች አልፎ በመግባት ተጠረቃቀመ ። ከጥቂት ግዜ በኋላ ፤ እኔም እንደዚያዉ አደረግኩ ። ወደ መጠለያዬ እንደተመለስኩ ፤ በዚያን ዕለት

## ትናንትና

የሚቀጥለዉ ቀን ዓርብ ሲሆን የገና በዓል የዋለበት ነበር ። የደኅንነት ኃይሎችም በዕለቱ "ድንገተኛዉን" ወረራቸዉን ደገሙት ። ይህኛው ግን ለወትሮዉ " አናርኪስቶችን የመመንጠር" ዘመቻ ብለዉ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተለየና ህጋዊነት የተሰጠዉ ግብረ ዘረፋ ቢባል የሚቀልል ክንዉን ነበር። ዕለቱ አንድም ፤ ለሱቅ ግብይትት የሚያመቹ ዕድሎች ያልነበሩት ከመሆኑም ወዲያ በእስራቱ፤ በግድያዉ፤ በእንግልቱ... ወዘተ ያልተነካ ቤተሰብ አልነበረምና ፤ በአብዛኛዉ ሰዉ ዘንድ ከዓመት በዓል የተቆጠረ አልነበረም ።እንደ እዉነቱ ከሆነ በየመንገዱ የሚታየዉ ከባባድ የጦር መሣርያና የከበባ ስሜት የዐዉደ ዓመቱን መንፈስ አዳፍኖታል ።በጭነት መኪና ታጭቀዉ፤ ለፋሺስቶቹ አለቆቻቸዉ ዉዳሴ በሚዘምሩና ለተርታዉ ሕዝብ ደግሞ ማስፈራሪያ ቃላትን ከአፋቸዉ በሚያዥጎደጉዱ ወታደሮች ዕይታ የዐዉደ ዓመቱ ድባብ ተበለሻሽቷል ።

በጭምጭምታ የሚሰማዉ የተለያየ ነዉ ። አንዱ ፤ "የእመቃዉ ዘመቻ ተረኛ ዒላማ የፒያሳ አካባቢ ነዉ፤"ሲል ፤ ሌላው ደግሞ "አረ በፍጹም፤ ካዛንቺስ ነዉ" ይላል ። ሌሎቹ ደግሞ ተቀብለዉ ፤ " ርግጠኛዉ ባለተራ የጉለሌ አካባቢ ነዉ ፤" ይላሉ ።የሕዝቡ ጠላቶች፤ በመላዉ አዲስ አበባ የሚገኙትን ፪፻፺፩ (ሁለት መቶ ዘጠና አንድ) ቀበሌዎች ለመመንጠር ያላቸዉን ዕቅድ በስዉር ለመያዝ ሲሉ ግራ የሚያጋቡ ጭምጭምታዎችን ዘርተዋል ። ሁኔታዉን ይበልጥ ያከፋዉ ደግሞ ፋሺስታዊዉ አገዛዝ " "ማሪኝ አብዮቴ" ብለዉ የተመለሱ" ወጣቶችን ቃለ ምልልስ በሬዲዮ ማስተላለፍ መጀመሩ ነበር ። ከእነዚህም አብዛኛዎቹ በተካሄደባቸዉ ስየልና ሥቃይ ተሸንፈዉ የቀድሞዉን ሰልፋቸዉን የለወጡ ናቸዉ። ከአዲሶቹ ወዶ ገቦች የተወሰኑት በአድርባይነት ፓርቲዉን ከድቶ የተሰነጠረዉና በድርጅታችን ላይ ከፍተኛ አደጋ ለማድረስ የተራወጠዉ አንጃ አባላት ነበሩ ።

ፋሺስታዊዉ አገዛዝ ፤ስለድርጅቱ አሠራር ዉስጣዊ ዕዉቀት በነበራቸዉ በነዚህ ወዶ-ገቦች መገልገል መጀመሩ ያልታሰበ ጠቀሜታ አስገኘለት ።የእመቃ ዘመቻዉም እየተጠናከረ የሄደ ሲሆን ፤ ይህ በበኩሉ በድርጅታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አስከተለ። እኔ በበኩሌ ፤ባለፉት ቀናት የተመሰቃቀለዉን ድርጅታዊ የግንኙነቴን መስመር መልክ መልክ ለማስያዝ ጥረት በማድረግ ላይ ነበርኩ ።ቅዳሜ ምሽት ላይ የሁለት የቅርብ ጓደኞቼ መኖሪያ ቤት አሰሳ ተደርጎበታል ።ጓደኞቼ በወቅቱ ያልነበሩ ቢሆንም ቤታቸዉ ግን ብርበራ ተካሄዶበታል ፤ ተዘርፏልም ። ተሸሽጌ ከምኖርበት ቤት እንደደረስኩ አስጠጊዎቼ እኔንና እንደኔዉ ተሸሽጋ ከዚያዉ ቤት የምትኖረዉን ሌላይቱን ሴት ጓድ ለደኅንነታችን ስንል አካባቢዉን ለቅቀን እንድንሄድ መከሩን ።የኤርትራ ተወላጆቹ አስጠጊዎቻችን እኛም ሆነ ራሳቸዉ በጋራ የገባንበት ሁኔታ ከመጠን ያለፈ አስጨንቋቸዉ ነበር ። ከዕለት ወደ ዕለት በአካባቢዉ የሚፈጸመዉ ሁሉ በጎ ነገር እንደማይመጣ የሚያመለክት በመሆኑ የተነሳ የቤተሰቡ አባላት የነበሩት ሁለቱ ወጣት ሴቶችም መኖሪያቸዉን መለወጥ ግድ ሆኖባቸዋል ።

ይቀጥላል..........


## የቶምቦላ ቲኬት በመግዛት ፍኖተ ዴሞክራሲን ይርዱ



# ነጻ ሀሳብ

## <u>ከህዝብ ውጭ ስልጣን አይገኝም! ቢገኝም አይረጋም!</u>
## <u>እንኳን ለ44ኛው የትግል ዘመን አደረሰን!</u>

(በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ የተላለፈ ሐተታ)

ሥልጣን በቅድሚያ የህዝብን ይሁንታ የሚያገኙበት፣ ለህዝብ ታማኝ ሆኖ ለመገኘት ቃል የሚገቡበት፣ ለህዝብ የሚሰሩበት፣ ለህዝብ አገልጋይነትን የሚያስመሰክሩበት እንጂ! በህዝብ ላይ የሚሾሙበትና የሚያታልሉበት ማጭበርበሪያና መኮፈሻ ካባ አይደለም።

በመሆኑም ነው ህዝብ እራሱ የሚበጀውን ለይቶ አውቆ ይምረጥ የሚባለው። በስልጣን መባለግ በኢትዮጵያ ለዘመናት የቆየ ህዝባዊ የትግል መፈክር ነው። በእርግጥ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዳይሆን በተቃውሞ የቆሙ ሀይሎች ሲያጨናግፉት ቆይተዋል። የውጭ ጠላቶችም ተባባሪ በመሆን ሲያደራጁዋቸውና ለስልጣን ሲያበቁዋቸው ተስተውሏል። ይህ ሁሉ የሆነው ግን ህዝብን በማጭበርበርና በማታለል ነው። የወያኔ ስልጣን ላይ መውጣት የነዚህ ሁሉ ውጤት ነው። በመሆኑም በህዝብ ፈቃድ ያልተመረጠ ሀይል በይስሙላ ምርጫው የምርጫ ኮረጆ እየገለበጠ 25 ዐመታት ለመቀመጥ ችሏል። ዕውቅና የሚሰጡት የውጭ መንግስታትም ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንደሆነ ከወያኔ የአገዛዝ ዘመን በላይ አስረጅ አያስፈልግም።

እንደወያኔ አይነት በህዝብ ላይ እምነት የሌላቸው ገዥዎች ካልተገደዱ በስተቀር በፍቃዳቸው ስልጣን ለህዝብ አስረክበው አያውቁም። ህዝብ የተነጠቀ መብቱን ለማስመለስ የተራዘመ ትግል አድርጓል፣ እያደረገም ነው። ለጊዜው ይውተርተሩ እንጂ! በህዝብ አቸናፊነት እንደሚደመደም ጥርጥር የለውም። በየመንግስታቱ ስር የተወተፉ ፍርፋሪ ለቃሚዎች በንጉሱም በደርግም ዘመን ተስተውለዋል። የግለሰብን ፈላጭ ቆራጭነት የሚያውጁትም እነዚሁ ለግል ጥቅም ያሰፈሰፉ ግለሰቦች ናቸው። ጀግና የህዝብ ልጅ፣ አርበኛ ወጣትን በቀይ ሽብር አስጨፍጭፈው ሀገርና ህዝብን ከመከራ ውስጥ የከተቱ እነዚሁ ሆድ አደር ባንዳዎች ናቸው። በስማቸው ሲጠሩአቸው ተሰደብን ብለው ይንጫጫሉ። ስምን ድርጊት እንደሚገልጠውና እንደሚያጋልጠው ዘንግተው።

የጠላት መሳሪያ ሆነው በዘመናዊ ባንዳነት ተሰልፈው የህዝብን ሀብት እየቀሙ በኢንቨስተርነት ስም በሀገር ላይ የሚቀልዱና የሚያስቀልዱ እነማን እንደሆኑ ህዝብ ይጠፋዋል ብለው ከሆነ ጅሎች ናቸው። ህዝብ ሁሉንም ነገር ያውቀዋል። በመሆኑም ነው የህዝብ ጠላቶች፣ ኢህአፓ የህዝብ ጠላት ነው ብለው ሲሉ ስቆ የሚያልፋቸው። ኢህአፓ ከህዝብ ልብ ውስጥ መሆኑን ላላወቁ እናዝንላቸዋለን። ኢህአፓ ከህዝብ ተነጥሎ አያውቅም። ሲራብ እየተራበ፣ ሲቆስል እየቆሰለ፣ ከጎኑ ሆኖ የህዝቡን ሰቆቃ አብሮ የሚካፈል ድርጅት ነው። ኢህአፓ ለህዝብ ሲሞት ሲረሸን፣ ሲታሰር፣ ሲሰደድ፣ ሲንገላታ እንጂ ከጠላት ዕርዳታ ለምኖ በህዝብ ላይ ልሾምብህ ብሎ ሲያስቸግረው ህዝብ አያውቀውም። እንኳን መፅሀፍ ጦርም ይዘው ቢመጡ ኢህአፓንም ህዝብንም ዳግመኛ አያጠቁትም።

እርግጥ ነው ህዝብ ሲጠቃ ኢህአፓም ይጠቃል። ከህዝብ ጋር ይኮሰምናል፣ ከህዝብ ጋርም ይፈካል። የኢህአፓና የኢትዮጵያ ህዝብ ልደትም ሞትም አንድላይ ነው። እነዚህ የህዝብና የሀገር ጠላቶች ያልገባቸው ያ! ነው። ችግር የለውም ቀስ እያለ ይገባቸዋል። ለሆዳቸው፣ ለጥቅማቸው እንጂ! ስለህዝብ የማይጨነቁ ናቸው። መንገድ ላይ ወድቆ ከሚያዩት ወገናቸው ይልቅ የውጭ ኢንቨስተሮች የገነቡት ፎቅ ይታያቸዋል። የዛሬውን የህዝብ ረሀብና ሰቆቃ በማይጨበጠው የምርት መትረፍረፍ ፕሮፓጋንዳ በተስፋ ዳቦ ጠግበን እንድንቦርቅ የነገን ብሩህ ገፅታ ሊያሳዩን የሚጥሩት ተደጋፊዎች ህዝብን ሊያሳስቱ <u>ሽር ብትን</u> እያሉ ነው። "ችግር ከሁዋላዬ ሰባ ብር ከፊቴ እስመ በተስፋሁ <u>ሀደረ</u> ስጋዬ"(ላልቶ ይነበብ) ብለን እንድንፈጠም ማለት ነው።

ወያኔና ግብረበላዎቹ ከወንጀል ሁሉ የከፋው ወንጀላቸው ሀገርን ለባዕዳን እያስረከቡ፣ ንብረትን እየቸበቸቡና እየተከፋፈሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ለዘላቂ ችግርና፣ መከራ ዳርገው እነሱና ልጆቻቸው እየተዝናኑ ለመኖር የሚያደርጉት ያልተቋረጠ ሩጫ ነው። ወጣቱ ይህንን በሚገባ ያውቀዋል፣ ማወቁም ተገቢ ነው። ሀገሩን እሱም ሆነ ልጁ ከሰማንያና ዘጠና ዐመታት የሊዝ ኪራይ ዘመን በሁዋላ መልሶ እንደማያገኛት አውቆ አሁኑኑ በመረረ ትግል ወያኔን ማስወገድና የባለ ሊዞችን ውለታ ማደስ ወይም መሻር ማስፈለጉን የተረዳና ሀገራዊ ግዴታውን ለመቀበል የተዘጋጀ ወጣት፣ ኢትዮጵያ ያስፈልጋታል። ለዚህም ዝግጁ መሆኑ የሚያስደስት ነው። ወያኔ ያዘናጋቸውም ዜጎች ቢኖሩ፣ ጥቅማጥቅም ከዘለቄታዊ የሀገር ህልውና በላይ የሚታይ አለመሆኑን ተገንዝበው አስተዋይ ወንድሞቻቸውን ይቀላቀሉ። ይህን ለማድረግ በረሃ መውረድ አያስፈልግም። በያሉበት ሆኖ ሀገርን መታደግ ይቻላል።

የኢህአፓ አባላትና ደጋፊዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ድሉን እስኪቀዳጅ ድረስ በተሰዉት ጓዶቻቸው ስም ቃል ኪዳናቸውን እያደሱ፣ በድርጅቱ ውስጥ ሆነው ትግላቸውን ይቀጥላሉ። የህዝብን ጠላት ይመክታሉ እንጂ! አያፈገፍጉም። "መዝሙራችን ትግሉ ነው ህይወቴ" ድርጅታችን ሀቀኛው ኢህአፓ ነው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ጠላቶች በኢህአፓ ላይ ዘመቻ እያካሄዱበት ቢሆንም ኢህአፓንና ህዝብን መለያየት አይችሉም። ቢችሉ ኖሮ እስካሁን ያደረጉት ፕሮፓጋንዳ ሁሉ በሰራላቸው ነበር። በህዝብ ላይ ደባ ሰርቶ በህዝብ መታቀፍ አይቻልም። የኢትዮጵያ ህዝብና የኢህአፓ ጠላቶች እንደ ጉም ተነው ይጠፋሉ።

ህዝብ አቸናፊ ነው!
በትግላችን የሀገራችንን የተቀማ ክብር እናስመልሳለን!!
እንኳን ለ44ኛው ዓመት የትግል ዘመን አደረሰን!

//

## <u>ታጥቦ ጭቃ--ቢከፍቱት ተልባ</u>

ከጸሓይ በታች አዲስ ነገር የለም ለማለት ባይሆንም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ውጣ ውረድ ድግግሞሽ መኖሩ የሚካድ አይደለም ። ለምሳሌ ሕዝብ ድሉን ሲነጠቅ የመጀመሪያው አይደለም ። አሁንም በወያኔ መቃብር ላይ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ ወይም መልኩን ቀየር ያደረገ ወያኔ ሊያስቀምጡ ደፋ ቀና የሚሉ አልጠፉም ።

የአዲስ አበባው ቤተ መንግሥት ልክፍት ሊሆን ይችላል ሲባልም ተደምጧል ። ባለስልጣን ሆኖ እዚያ የገባ ያለፈውን፣ የወደቀውን፣ ከፉና ጨቋኝ የተባለውን መስሎ መገኘቱ አልቀረም ። ታገልኩለት ያለውን መርህ ጥሎ፤ የነበረውን አድሶ ይቀጥለዋል ። ወያኔና ደርግ በጣም ተመሳሳይ ጸረ ሕዝብ ሀይሎች መሆናቸውን ያጤኗል ። የፊተኛው ሀገር ልገንጥል ብሎ ባይነሳም ሕዝቧን ጨፍጭፎ ኢትዮጵያን ለግንጠላ አመቻችቶ ፍርጠጣን መርጧል ። ሁለቱም ጸረ ኢትዮጵያ አገዛዞች ነበሩ፤ ናቸው ቢባል ትክክል ነው ። ወያኒና ሻዕቢያም ተመሳሳይ ናቸው ። መለስና ኢሳያስ መንታዎች ናቸው ። ሟቹ የቅርብ ጓደኞቹን (እነ ተክሉ ሓዋዝን ለምሳሌ ) ሲገድል፤ የታሰሩ የኢሕ ፓ መሪዎችን ሲረሽን ኢሳያስ ደግሞ የቅርብ ጓዶቹን አሰቃይቷል፤ አባክኗል ። አገዛዛቸውም ጨቁኝና አፋኝ መሆኑን ማንም የሚመሰክረው ሲሆን ወያኔ ለፈረንጆቹ በማደር በኩል ቀልጠፍ ብሎ በመገኘቱ የአስመራውን ያህል መጋለጥና ጥቃት አልደረሰበትም ። ወያኔ ተባለ ሻዕቢያ ግን ያው ቢከፍቱት ተልባ ለመሆናቸው ክርክር አይፈልግም ።

የድግግሞሹ--ታጥቦ ጭቃነት--ደግሞ ተቃዋሚ ነን ያሉትንም ቀስፎ እንደያዘ ጥርጥር የለውም ። የተሳሳተ አቅዋማቸውን ሙጥኝ ብለው ደርቀው ይዘው ወደዱም ጠሉም ለወያኔ የስልጣን ዘመን ጥቃሚ ሆነው አሉ ። ሕዝብን የሚለያይ መፈክርን ማቀፉ ስህተት ሆኖ ሳለ መቀየር ሀጢያት ነው ያሉ ይመስል --የሞኝ ነገር መልሶ መላልሶም ማለት ይቻላል--በስህተታቸው ዙሪያ ጮቤ በመርገጣቸው ውጤታቸው ወያኔን መጥቀም ሆኗል ። በቅርቡ ለምሳሌ 4 የኦሮሞ ድርጅቶች ተስማማን ብለው ባወጡት መግለጫ ትግላችን ነጻ ኦሮሚያን ለመመስረት ነው ብለው አስፍረዋል ። እንኳን ብዙሃኑን ኢትዮጵያዊ ቀርቶ ብዙሃኑን ኦሮሞ የማያቅፍ አቅዋምን እንደ አዲስ ማናፈስ ከስህተትም በላይ ነው ። በአንጻሩ ደግሞ ያበቃና ወግድ የተባለ የትምክህትና ጸረ ዲሞክራሲ አገዛዝን/ስርአትን ለመመለስ የሚመኙና ጻያፍ ፕሮፓጋንዳም በሕዝብ ላይ የሚያሰሙ ተስፈኞች ዛሬም አሉ ። የደርግ-ኢሠፓ ሞትን ለመሰረዝና ነፍስ ሊዘሩበት ብቅ ያሉት በዚሁ ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው ። የማይሆን ነገር ይሆናል ብሎ መዳከር ከንቱ ልፋት እንደሆነው ሁሉ ወደ ድል ሊወስድ እምቢ ባለ ስልትና መንገድ፤ አቅዋም ይዞ መልፋቱም ውጤት አልባ ከመሆን አያልፍም ። ታጥቦ ጭቃነትም ነው ። ተሻሻሉ፤ ከተምክሮ ተማሩ፤ ድክመታቸውን መርምረው አስወገዱ ልንልን በምንፈልግበት ጊዜ ለዓመታት ያነሆለለ ስህተት መድገም ማለት ነው ። ያሳዝናል።

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ከገጽ 6 የዞረ

ፖለቲካ የምርጦች ነው ባይባልም  ማንም ዘው ብሎ የሚንቦጫረቅበት ግን አይደለም ። ዕውቀት ችሎታን ይጠይቃል ። የጡረት ጊዜ ስራ ወይም መዝናኛ አይደለም ። አንዳንድ ምሁር ተብዬዎች ፖለቲካን በጡረታ እንቅስቃሴ ደረጃ ስለወሰዱት በመድረክ ብዙ ችግርን ፈጥረዋል ። መምራት ያልቻሉ ወይም በፖለቲካ ምርጫቸው ከጸረ ሕዝቦች ጋር የከረሙም ምንም ለውጥ ሳያደርጉ አሁንም ግንባር ቀደም ቦታ ይሰጠን ብለው በሕዝብ ላይ ሊፏልሉ ሲፈልጉም ታይተዋል ። የታጠቀና የደረጀን ጠላት በዕውቀትና ስልት አልባ ትግል ማሸነፍ አይቻልም ። ለፈረንጅ ፈተና ስንት የሚያጠኑና የሚመርመሩ የሀገራችንን ሁኔታ በሚመለከት ግን እንደ ሰነፍ ተማሪ በአቦ ሰጥ ሊወጡት ሲጥሩም ታይተዋል ። ፖለቲካ ሳይሆን ሕዝብ ቦተለከ የሚለው መከተሉ የሚጠበቅ ነው ማለትም ይቻላል ። ፖለቲካን ማውቅ፤ መቻል፤ ለመንቀሳቀስም መቻል ይጠይቃል ። ወያኔ ስንቱን ተቃዋሚ አደናግሮና አወናብዶ፤ስንቱን የተቃዋሚ መሪ አቃጥሎ ከጥቅም ውጪ ግን ያደረገው መሪዎች ነን ባዮቹ ስለ ፖለቲካ፤ማለትም ስለ ወያኔ ይዘትና ስለ ተጨባጬ ሁኔታ (ሀይሎች አሰላለፍ ወዘተ) በቂ ግንዛቤ ስለገኀደላቸው ነው ። ይህን ግን ሀቅ ብሎ ማመን ግን ቀላል ሆኖ አልተገኘም ።የአመራር እንጂ የአባላት ጉባኤ ለዘመናት ያላደረገ ድርጅት አለ ። የአባላትና የሕዝብ ድምጽ እይደመጥም--በመሆኑም የምርጦቹ ፍላጎትና ውሱን ዕምነት የድርጅት አቅዋም ሆኖ ሰፍኖ ቆይቷል ። መሻሻልና መለወጥ አልተቻለም ።

ታጥቦ ጭቃ፤ቢከፍቱት ተልባ!!  ተልባ እንኳን ጥቅም አለው ።

# እንኳን

# ለ44ኛ ዓመት

# የኢሕአፓ  ምስረታ በዓል

# በሰላም  አደረሳችሁ

## ፍካሬ ዜና
## አጫጭር ዜናዎች

ገጽ 4 የዞረ

**<u>የወያኔ ምርጫ ቦርድ የአስራ አራት ፓርቲዎችን ፍቃድ መሰረዙ ታወቀ፡፡</u>**

- ወያኔ ምርጫ ቦርድ በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት አስራ አራት የወያኔ ተቃዋሚ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን ፍቃድ መሰረዙን አስታውቋል፡፡ ወያኔ አሁን ፍቃዳቸው መሰረዙን ይፋ ያደረጋቸው ድርጅቶች በተለያየ መንገድ እያዳካማቸውና እያሽመደመዳቸው እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ከእነዚህ ከተሰረዙት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት እንደሆነ ታውቋል፡፡ ይህ ድርጅት የተመሰረተው በ1997 ዓ.ም. የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በህብረት ለመታገል በተስማሙበት መሰረት መሆኑ አይዘነጋም፡፡ ኢሕአፓ የዚህ ህብረት አባል በመሆን የበኩሉን ጠንካራ ተሳትፎ አድርጎ እንደነበር ብዙዎች ያስታውሳሉ፡፡

**<u>ወያኔ እራሱ በቀሰቀሰው ቀውስ አገሪቱ ላይ ስጋት እንዲያንዣብብ ማድረጉ ተገለጸ፡፡</u>**

- ወያኔ ሕዝብን በዘር፣ በሀይማኖት፣ በጎሳ በጎጥ ከፋፍሎና ሕዝብን እያፈነና እያሰረ ሕዝብን ማሸበር እንደ ዋነኛ መሣሪያ በመጠቀም 25 የግፍ አገዛዝ አመታት አሳልፏል፡፡ ወያኔ እራሱ በፈጠረው የጎሳ ፖለቲካና የግፍ አገዛዝ ዘመኑን ለማርዘም ካለ በቂ ጥናት በርካታ ሕዝብን የሚጎዱና የሀገርን አንድነት የሚንዱ እኩይ ተግባራትን እየፈጸመ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ከወያኔ ውስጥ አወቶች የሚወጣው መረጃ የሚያስረዳው ወያኔ በስጋ መወጠሩን ነው፡፡ በትግራይ ወርቅ አውጪዎች ታፍነዋል፡፤ በጋምቤላ ታፍነው ከተወሰዱት ህፃናት እስካንሁን ከሰማንያ ከመቶ በላይ የሚሆኑት አልተመለሱም፡፡ በቅርቡ ቤንሻንጉል ድንበር አካባቢ እርሻ ላይ የነበሩ ገበሬዎች ከሱዳን ድንበር ዘለው በገቡ ታጣቂዎች ታፍነው ተወስደዋል፡፡ እስካሁንም በወያኔ በኩል ምንም የተባለ ነገር አለመኖሩ ሕዝቡን መስቆጨቱ ታውቋል፡፡ ወያኔን እያተራመሰ ያለው ግብፅ ሙሉ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ እግረኛ ጦሯን ሰሜን ሶማሌ ሀርጌሳ ላይ ማስፈሯ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በተለያዩ አካባቢዎች ለሚከሰቱ የፍንዳታ አደጋዎችና የታጠቁ ኃይሎች እንቅስቃሴን ከኤርትራ ጋር በማያያዝ ያቀርብ የነበረው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግብፅን ሊጨምር እንደሚችል እነዚሁ ወያኔ ውስጥ ያሉ ይህን መረጃ ያደረሱን ያስረዳሉ፡፡

**<u>ግብፅ የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅሟን በእጅጉ እያሳዳገች መሆኑ ታወቀ፡፡</u>**

- የግብፁ አህራም ጋዜጣ እንደዘገበው በአሁኑ ሰዓት ግብፅ የነበራትን 32 ሺ 15 ሜጋ ዋት ሰሞኑን ግንባታቸው ተጠናቆ ሥራ የጀመሩት ሲጨመሩ 35 ሺ 615 ሜጋ ዋት የሚያመነጭ ኃይል እንዳላት ተገልጿል፡፡ አትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የምታመርተው ከ2 ሺ 400 ሜጋ ዋት በላይ እንደማይበልጥ የታወቀ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከንፋስ ኃይልና በቅርቡ ግንባታው እንደተጀመረ የተነገረለት የግልገል ግቤ 3 እና ቅዠት የሆነው የዓባይ ግድብ ከተጠናቀቁ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ኃይል ከአስር ሺ ሜጋ ዋት በላይ እንደማዘል የታወቀ ነው፡፡ የሚገርመው ወያኔ ከግብፅ ጋር በዓባይ ግድብ ላይ ለገጠመው ግብግብ እያቀረበ ያለው ከግድቡ የሚወጣውን ኃይል ሃምሳ ከመቶ የሚሆነውን ሱዳንና ግብፅ እንዲጠቀሙበት ለመደራደሪያነት ማቅረቡ ነው፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የግብጽ ኢጂሳት የሚባለው የስለላ ሳተላይት በአባይ ላይ ይሰራል የተባለውን ግድብ በቅርብ እየተከታተለ መሆኑ ሲነገር በግድቡ ላይ ዋና ስራ መቆሙን ወይም መጓተቱን ለመሰለል መቻሉም ተዘግቧል ።



በኖርዌይ የምንገኘ ወጣቶች ኢሕአፓን የተቀላቀልንበት ምክንያት ድርጅቱ ጥርት ያለ ዓላማ ያለው ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ለመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲ፣ ለሕዝብ መብት መረጋገጥና በእኩልነት ለተመሠረተ አንድነት ታግሎ እያታገለ ያለ ድርጅት በመሆኑና ያለፉትንም ሆነ የአሁኑንም አምባገነን ሥር አቶች በመቃወም መሥዋዕትነት የከፈለና እየከፈለ ያለም ድርጅት በመሆኑ ምንም እንኳን ትግሉ እየተራዘመ ቢመጣም አይቀሬውን ሕዝባዊ ድል ለመቀዳጀትና በተለይ ኢትዮጵያን ለመበተን ሳይታክት እየሠራ ያለውን የወያኔ ቡድን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ብሎም ትግሉን ለማስቀጠል መፍትሔው በተለይ የህብረተሰቡ ትኩስ ኃይል (ወጣቱ) ሊጫወት የሚችለው ሚናና አስተዋጽኦ ትልቅ ሊሆን ስለሚችል ወጣቱ ኢሕአፓን እንዲቀላቀል ጥሪ እናደርጋለን !!

**ዳዊት ተምስገን ኢሕ አፓ ወጣት ክንፍ (ኢወክንድ)**

**ኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ ኖርዌይ)**



አንኳን ለኢሕአፓ 44ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል አደረሳቹ ሥል.... ተ/ክለሃይማኖት በታች ያለዉ 44 ቀበሌ የተሰዉትን በከፊል ሳነሳ ደስታዬ ወሰን የለዉም። ከተፈቀደልኝ የኢሕአፓን ጎዳና የመራችኝ ዛሬ በህይወት የሌለችሁን ጓዲት ማዉባ እድሪስ፣ በክብር ያለፉትን ጀግኖቻችን ጌታቸዉ እሸቱ፣ ገርማ እሸቱ፣ ፈጠነ እሸቱ፣ ጳዉሎስ ወርቁ፣ አበራሽ ወርቁ፣ መሃመድ ሙዘይን፣ ሙደሰር ሁስማን፣ አህመዲን (ዶሮ) ሽንቁጤ ሳህሌ፣ ስብስቤ ሃይሌ፣ ጌታቸዉ ዘንጋዉ ወዘተረፈ...... ለአናተ የሚመጥን ህዉልት ኢሕአፓን ህልዉ አድርጎ መጓዝ ነዉና እነሆ ዛሬ 44ኛ አሙቱን አክብረን የኢትዮጵያ ነፃንት እስኪከበር የተሰዋችዉላት ኢትዮጵያንና ህዝብዋን ሳንከዳ ቃል ሳናጥፍ ትግሉን ቀጥለናል. አብሽሩ ጓዶች።


**ዮሐንስ ታከለ (ነባር የኢሕአፓ አባል)**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ክአንዱ አምባግነን ወደ አንደኛው አምባገነን እየተሸጋገረ እነሆ ፍዳውን እየበላ ነው፡፡ ይህንንም ግፍና በደል ለማስቆምና ሕዝባዊ ሥርዐት ለመመስረት ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ



እንሆ ለአርባ አራት ዓመታት ከአካል እስከ ብርቅ ህይወት በመክፈል ታግሏል እየታገለም ነው፡፡ ትግሉ መራራና አሰልቺ ቢሆንም ያለ መታከት ሕዝባችንና ሀገራችንን ከአምባገነኖች መዳፍ ለማላቀቅና ነፃነቱን ተጎናፀፎ የሰላምና የዓንድነት ብሎም የፍቅር አየር እስከሚስብ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል፡፡ እንኳን ለአርባ አራተኛው(44ኛው) የምስረታው በዓል አደረሰን


**አሊ ሁሴን (የሶሴፐ ሊቀመንበር)**



በሰሜን ፣ በደቡብ ፣ በምስራቅና በምዕራብም በተለያዩ ክልሎች ፣ ህዝቡ ከዚህ አፋኝ አገዛዝ ለመላቀቅ ትግሉን በማቀጣጠል ላይ ባለበት በዚህ ወቅትና ህዝባዊ ትግሉ፤ ከመቼውም በበላይ ቆራጥና በጠላቱ ላይ የማያወላውል፤ ግንባር ቀደም መሪ በሚሻበት ወቅት፤ የሚከበረው ይህ 44ኛ የምስረታ በዓላችን ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው ብዬ አምናለሁ። ኢህአፓ/ሠ በረጅሙና አስቸጋሪው ትግሉ ብዙ መሰናክሎችን አልፎ እዚህ ደርሷል።

ይህ ሁሉ መስዋዕትነት ፣ የፈሰሰው ደምና የተከሰከሰው አጥንታችን በከንቱ አልነበረም፤ ለምንወዳት ሀገራችን ነፃነትና ለህዝባችን መብትና ፍትህን ለማጎናፀ እንጂ። እንደሚታወቀው፣ ኢህአፓና ሠራዊቱ ኢህአሠ ፣ ከመላው የሀገሪቱ ክፍሎች በዘርና ሀይማኖት ሳይለያዩ ለአንድ ዓላማ በአንድነት ተሰልፈው የተዋደቁ ጀግኖች ያቀፉ ነበሩ ናቸውም ፡፡

**ወንድሙ ነጋ (የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴ አባል)**



እንኳን ለ44ው የኢሕአፓ ምሥረታ በዓል ሁላችንንም በሰላም አደረሰን!
በተሰዉት ጓዶቻችን ሰማዕታት የጀመርነውን ትግላችንን በቆራጥነት እንቀጣለን! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! እናቸንፋለን::

**አማረ መኮንን (ነባር የኢሕአፓ አባልና የአውስትራሊያ የኢሕአፓ አህጉራዊ ኮሚቴ አመራር አባል)**

ኢትዮጵያችን አንዳችም የውጭ ወራሪ ያልበገራትና የዓለም ጥቁር ሕዝብ ኩራት ሆና ሳለ አለመታደል ሆኖ ካብራኳ የወጡ ወያኔና የወያኔ የዘረኝነት ልክፍት የተጋባባቸው ድርጅቶች እንዲሁም በነዚህ ከሃዲ ድርጅቶች በስተጀርባ ሆነው የሚሰሩ የውጭ ሃይሎች በመተባበር ዛሬ አገራችንን አስቸጋሪ ከሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ሊከቷትን እየተጣደፉ ይገኛሉ። ኢሕአፓ ይህን ሴራ ገና ከጽንስሱ ጀምሮ የተገነዘበውና ሴራቸውም እንዳይሰምር የኢትዮጵያን ሕዝብ እያነቃና እያደራጀ ግንባር ቀድም ደጀን በመሆን ትግሉን ተያይዞታል። ድርጅታችን የደርግን ቀይሽበር፣ ፈታኝ የሆኑ የአንጃዎችን ብተናና የወያኔን እመቃ በመበጣጠስ ለወገን ሁሉ ኩራት ሆኗል።

ዛሬ 44ኛ የልደት በዓሉን የሚያከብረው ኢሕአፓ ትግሉ ገና ብዙ ጉዞ እንደሚጠብቀው ያምናል። መሬት የአራሹ ገበሬ ንብረት ገና አልሆነም፣ ለዘመናት የምንዋደቅለት የሕዝባዊ መንግስት እውን አልሆነም፣ ዲሞክራሲ ያለገደብ ምኞታችን የሰማይ ያህል ርቆናል፣ የሰበዓዊ መብት ጥሰቱና ረገጣው በዋልጌው የወያኔ ጥርቅም መንጋ ቀጥሏል። ኢሕአፓ ሕዝቡ ነጻ እስኪወጣ ድረሰ የጀመረወን ትግል በፍጹም አያቆምም፡፡ ላለፉት 44 ዓመታት በሕዝብ መሃል በመሆን የሕዝቡን ስቃይ እየተሰቃየና የሕዝቡን ሞት እየሞተ ይገኛል። የ44ኛ አመት ልደቱን ሲያከብር ሕዝቡ ነጻነቱን በእጁ ስር እስከሚያስገባ ድረስ ትግሉን የሚቀጥል መሆኑን ቃል በመግባት ያረጋግጣል።

አይበገሬው የኢሕአፓ አባላት በያላችሁበት፣ መከራ፣ ችግርና ድካም ሳያሸንፋችሁ አመራር ለምትሰጡን የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የሰሜን አሜሪካ እሕጉራዊ የኢሕአፓ ኮሚቴ እንኳን ለ44ኛው የልደት በዓል አደረሳችሁ በማለት ደስታውን ይገልጻል።

**ከሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ አሕጉራዊ ኮሚቴ**

**የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ የሳተላይት መስመር**

Channel Name : Finote Democracy
Satellite : Telstar
Azimuth : 15 deg West
Frequency : 12.550 MHz
Polarity : Horizontal
Symbol rate : 4411
FEC : 2/3

**የፍኖተ ዴሞክራሲ በስልክ ማዳመጥ ይቻላል**

USA 712 832 7010
Germany 30 1388 0065
Sweden 8 4030 8871
Australia 2 8072 5180
UK 0330 332 6500
Norway 47 2193 9609
Netherlands 20 262 1096
Israel 23 721 012
Canada 867 675 0263
Kenya 205 293 342

**ፍኖተ ዴሞክራሲን በስማርት ፎን አፕሊኬሽን በማውረድ መስማት ይቻላል**